የሰ/መ/ቁ. 97555

ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ወ/ሮ ሳኒያ ከድር ጠበቃ ዘካርያስ መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኮሪያ ዘማቾች ቤተሰቦች ሽመናና ስጋጃ ስራ ጠበቃ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሣሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ይዘቱም በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የሁከት ይወገድልኝ ክርክር ክስ ለመስማት በተቀጠረበት ቀን እንደማንኛውም ሰው ፍርድ ቤት ቀርቤ ተራዬን እየጠበቅኩ ስሜ የተጠራ መስሎኝ በሌላ ሰው መዝገብ ችሎት ገብቼ  የእኔ ያልሆነው መዝገብ ሲዘጋ የእኔ መስሎኝ በመሄድ የእኔ መዝገብ ሲጠራ ባለመቅረቤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይህ የሆነው ባለመስማትና ባለማሰብ በጥፋቴ ስለሆነ የተዘጋው መዝገብ ይንቀሳቀስልኝ በማለት ሲሆን ተጠሪዎችም የአመልካች ጥያቄ ደርሶአቸው በሰጡት መልስ(ሀሳብ)አመልካች በራሳቸው ጥፋት መዝገቡ መዘጋቱን ስለገለፀው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ እንደዚህ አይነቱን ጥፋት ይቅርታ የሚያደርግበት አግባብ ስለማይኖር መዝገቡን ለማስከፈት በቂ ምክንያት አይሆንም በቸልተኝነታቸው በመሆኑ ሊንቀሳቀስ አይገባም ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ክርክር ከፍ/ብ/ሥ/ሥህቁ. 74(2) አንጻር ለመመርመር ከላይ አመልካች ባለመቅረባቸው ምክንያት ነው ብለው የሰጡትን ሀሳብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጋችን በቂ የሆነ እክል ምክንያት ትርጉም ባይሰጠውም አመልካችን ከችሎት መቅረብ ያገደው ምክንያት በቂ እክል ሊሆን የሚችል አይደለም በማለት መዝገቡ ሊቀሳቀስ አይገባም በማለት ጥያቄው ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በይግባኝ የቀረበለትን መዝገብ በ22-4-2006 በዋለው ችሎት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡በአቤቱታቸውም ላይ የሥር ውሣኔዎች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን ቁጥር 74(2) አላማ ያላገናዘበ ትርጉም የተሰጠው ስለሆነና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልን ይገባል ሲሉ ጠይቋል፡፡

በዚህም የሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው አመልካች የሌላ ሰው ሥም ሲጠራ በስህተት ወደ ችሎት ገብተው መዝገባቸው የተዘጋ መስሏቸው መሄዳቸው በቂ እክል ምክንያት ነው?አይደለም የሚለውን ለመመርመር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካቀረቡት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንግዲህ አመልካች በዚህ ጉዳይ የሚሉት በፍ/ቤቱ ቅጥር ጊቢ መጥቼ ተራዬን በመጠባበቅ ላይ እያለሁ በስህተት የሌላ ሰው መዝገብ በተጠራበት ወደ ችሎት ገብቼ መዝገቡ የተዘጋ መስሎኝ መሄዴ በጉዳዩ መሣሣቴና ያለማሰቤን ይገልፃልና መዝገቡ ሊንቀሳቀስልኝ ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው እንደዚህ ያለው ስህተት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህጋችን እንደበቂ ምክንያት ሊቆጠር የሚገባው ነው አላለም ስለዚህ ሊንቀሳቀስላቸው አይገባም የሚል ነው፡፡የሥር ፍ/ቤቶችም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰሙ በኃላ አመልካች በንቃት መከታተል ነበረባቸው ጥፋት መሆኑን እራሳቸውም አምኗልና መዝገቡ ሊንቀሳቀስ አይገባም በማለት በብይን ዘግቶታል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የጉዳዩን አመጣጥ ሲመረምረው አመልካች ቀጠሮአቸውን አውቀው ወደ ፍ/ቤት ጊቢ መጥተው መሄዳቸው ተጠሪ በፅሑፍ ከሰጡት መልስም ሆነ የሥር ፍ/ቤቶች የተቀበሉት እውነታ ነው ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች በስም ስህተትና ባለማስተዋል ችሎት ገብቶ መዝገባቸው የተዘጋ መስሏዋቸው መሄድ በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብለው ጉዳያቸውን ትተው የሄዱ ናቸው ወደ ሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ተጠሪ እንደሚሉትም አመልካች ጉዳዩን ለመጎተትና ተጠቃሚ ለመሆን ሲሉ እያዩ ሄዱ የሚለው ክርክርም ከግምትነት በዘለለ የተረጋገጠም አይደለም፡፡በመሆኑም ችሎቱ ይህን አባባል አልተቀበለውም፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.74(2) ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማም የአመልካችን አይነት ተከራካሪ ወገን ለመገደብ ተብሎ የተቀረፀ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻልበት ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

በመሆኑም አመልካች ለመዝገቡ መዘጋት እንደ ምክንያት ያቀረቡዋቸው ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. (74(2) ሥር እንደ በቂ የእክል ምክንያት ሊቆጠር አይችልም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ማጣቱ መሠረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርዓታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ብይንና የፌ/ከ/ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስላቸው ያቀረቡት ምክንያት በፍ/ስ/ሥ/ሥ/ቁ. 74(2)መሠረት በቂ ነው ብለናል፡፡
3. መዝገቡ እንደገና ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ ከቆመበት ይቀጥል ብለን ጉዳዩን ለስር ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ይፃፍ፡፡
4. የግራ ቀኙ ውጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ኢ